**AEPAC**

American Ethiopian Public Affairs Committee

ሰኔ 16 ቀን 2014 ዓ ም

ኢትዮጵያ፤ በምእራብ ወለጋ ጊምቢ ወረዳ በሚኖሩ ንጹሀን ኢትዮጵያዉያን የአማራ ተወላጆች ላይ ስለደረሰው ዘርን መለያ ያደረገ አሰቃቂ የግፍ ጭፍጨፋ

የኢትዮጵያ አሜሪካዉያን የሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ (AEPAC)
መግለጫ

የኢትዮጵያ አሜሪካዉያን የሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ (AEPAC) ሊቀ መንበር አቶ መስፍን ተገኑ፤ በኢትዮጵያ ምእራብ ወለጋ፤ ጊምቢ ወረዳ በሚኖሩ ንጹሀን ኢትዮጵያዉያን፤ ዘርን ተኮር ያደረገ በአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰዉን የግፍ ጭፍጨፋ፤ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ድርጅት ጋር በጎን በመቆም በጥብቅ ያወግዛሉ፡፡ እስካሁን እንደሚደርሰው መረጃ ከሆነ፤ ምናልባትም እስከ አንድ ሽህ ሊደርሱ የሚችሉ፤ ንጹሀን ኢትዮጵያዉያን፤ በአብዛኛዉ ሴቶችና ህጻናት ያሉበት፤ ንጹሀን ኢትዮጵያዉያን ምንም ጥፋት ሳይኖራቸው፤ በዘራቸዉና በቋንቋቸው፤ በአማራነታቸው ብቻ እየተለዩ፤ የኢትዮጵያ ፓርላማ አሸባሪ ብሎ በሰየመው፤ እራሱን "የኦሮሞ ነጻ አዉጭ አርሜ" እያለ በሚጠራዉ ጨቃኝ ቡድን በአሰቃቂ ሁኔታ በግፍ ተጨፍጭፈዋል፡፡

አቶ መስፍን መግለጫቸዉን በመቀጠል "በንጹሀን ኢትዮጵያዉያን ላይ የሚደረጉ እንደዚህ አይነት አሰቃቂና የግፍ ጭፍጨፋወች፤ በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን፤ ረሀብን ጨምሮ በከፍተኛ ችግር ላይ በሚገኙበት በዛሬው አስቸጋሪና አሳሳቢ ወቅት መፈጸማቸው፤ ከፍተኛ ሀገር አቀፍ የሰብአዊና ማህበረሰባዊ ቀውስ ሊያስከትሉ ይችላሉ የሚል ስጋት በሀገር ቤትም ሆነ በዉጭ እንደሰፈነ ግልጽ ነው" ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም፤ የዜጎቹን ደህንነትና የሀገርን ሰላም መጠበቅ ተቀዳሚ ግዴታዉ መሆኑን ተገንዝቦ፤ በፓርላማ አሸባሪ ተብሎ የተወሰነብትን ይህን አረመኔ ቡድን ተቋቁሞ በማጥፋት፤ በየጊዜው በንጹሀን ላይ የሚያደርሰዉን ግፍና ጭፍጨፋ በማያዳግም ሁኔታ ለማስቆም፤ በቆራጥነት በመነሳት  የመሪነትና ጠባቂነት ኃላፊነቱንና ግዴታዉን በሚገባ እንዲወጣ በጥብቅ ድርጅታችን ያሳስባል ብለዋል፡፡

በተለይም ባለፉት በርካታ ወራት በትግራይ ሽብርተኛዉ ቡድን የተቀሰቀሰዉን ጦርነት አስከትሎ፤ ሁለቱም በሀገሪቱ ፓርላማ አሸባሪ ተብለው የተሰየሙት፤ "የትግራይ ነጻ አዉጭ ድርጅት (ህወሀት)" እና "የኦሮሞ ነጻ አዉጭ ድርጀት (ሸኔ)" በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ንጹሀን ኢትዮጵያዉያንን ደም አፍስሰዋል፤ በዘር እየለዩም ጨፍጭፈዋል፤ የሚያሳዝነው በንጹሀን ዜጎች ላይ ግፍ ከመፈጸም ምንም ወደኋላ ሊሉ አልቻሉም! ጭራሽ እየባሰባቸው መጣ እንጅ!

እንደምንም ተቋቁሞ፤ ይህን የማያቋርጥ ግፋቸዉንና ጭፍጨፋቸዉን ቶሎ ማስቆም ካልተቻለ፤ መዘዙ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይገደብ በመላዉ ምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛ ቀውስ እንዳያስከትል ያሰጋል ብለዋል አቶ መስፍን፡፡ ይህ ደግሞ የአሜሪካንንም ሆነ የሌሎችንም ምእራባዉያን ሀገራትን ጥቅም ሊጎዳ እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያም ሆነ በቀጠናዉ አስተማማኝና ዘላቂ ሰላም እንዲወርድ፤ እነዚህ ሁለት አሸባሪና የሰላም ጠንቅ የሆኑ ቡድኖችን በዚህም በዚያም ብሎ በንጹሀን ላይ የሚፈጽሙትን ግፍ ቶሎ ማስቆም የግድ ይላል፡፡ አሜሪካና ሌሎች የምእራብ ሀገራትም ከኢትዮጵያ ጎን በመቆም፤ እነዚህን የሰላም ጠንቅ የሆኑ ሁለት ድርጅቶችን ተቋቁሞ በማሳረፍ፤ በሀገሪቱ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት መንግሥት በሚያደርገው ያልተቋረጠ ጥረት፤ ትክክለኛና ፍትህ የሰፈነበት ድጋፋቸዉን ከመለገስ ወደኋላ ማለት የለባቸዉም ሲሉ አቶ መስፍን ተገኑ አሳስበዋል፡፡